## እግዚአብሔርን ማክበር ክፍል 2

### እግዚአብሔርን ማክበር በምን ይገለጻል?

እግዚአብሔርን ማክበር ከሚገለጽባቸው መንገዶች አንዱ እርሱ ያከበረውን ሰው በማክበር ለበላይ መሪ/ኃላፊ ተገቢ ክብር በመስጠት ነው፤ ዘዳ 4፡10

እግዚአብሔር ቃሉን ከሚያስተምርባቸው ምክንያቶች አንዱ ሰው እግዚአብሔርን የሚያከብርባቸው መንገዶች/ሁኔታዎች ለማሳወቅ ነው፡፡ እግዚአብሔር በቃሉ ባስተማረው መንገድ የሚያከብሩትን ደግሞ ያከብራል/ወሮታ ይከፍላል/ከፍ ከፍ ያደርጋል፡፡ የናቁትን ደግሞ እንዲናቁ ያደርጋል፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝብ አምላኩን የሚያከብርባቸው ሁኔታዎች/መንገዶች በዝርዝር በቀጣይ ትምህርት የሚቀርብ ሲሆን ለአሁኑ አንዱን መንገድ ብቻ ከዚህ ቀጥሎ ሰፍሯል፡፡

እግዚአብሔርን ከምናከብርባቸው መንገዶች አንዱ እርሱ ያከበራቸውን ሰዎች በማክበር ነው፡፡ እግዚአብሔር ያከበራቸው እነማን እንደሆኑ አውቀን ስናከብር ከእርሱ ጋር ህብረታችን ከመስተካከሉ ባሻገር አማኞች እርሱ ያከበራቸውን የተለያየ ኃላፊነት የሰጣቸው ሰዎችን ከቤተ-ክርስቲያን አባላት አንዳንዶቻችን ደጋፊዎች፣ ሌሎቻችን ተቃዋሚዎች ከመሆን በመውጣት የመንፈስ አንድነታችን ለመጠበቅ ይረዳልናል፡፡ አለበለዚያ አቋማችን የተለያየ ስለሚሆን መከፋፈልን ያስከትላል፡፡ እግዚአብሔር ያከበራቸው እነማን ናቸው?

አምላካችን ወሰን አልባ ታላቅ ቢሆንም ማንንም ሳይንቅ፣ ሰውን ሁሉ ያከብራል፡፡ ሆኖም ለብዙዎች በረከት/ጥቅም ይሆኑ ዘንድ በተወሰኑ ሰዎች ላይ የተለየ የክብር ቅባቱን ያመጣል፡፡ የሹመት ስፍራን/ሥልጣንን፣ ኃይልን፣ ጥልቅ እውቀትን፣ ጥበብን፣ ተናግሮ የማሳመን ችሎታን፣ የአመራር ችሎታን፤ መገለጥን፤ ልዩ ልዩ መንፈሳዊ የሆኑና ያልሆኑ ስጦታዎችን ይሰጣል፡፡

1ዜና 16፡19-22 ...ማንም እንዲጨቁናቸው አልፈቀደም፡፡ ስለ እነርሱ ነገስታትን ገሰጸ፡፡ የቀባኋቸውን አትንኩ በነቢያቴም ላይ እጃችሁን አትዘርጉ፡፡ (ዘካ 2፡8 የሚነካችሁ ያይኑን ብሌን ይነካል)፤

እግዚአብሔር ለእስራኤል ህዝብ መንፈሳዊና ፖለቲካዊ አመራር አጣምረው የሚሰሩ በቀጥታ በራሱ የሚመሩ ሰዎችን/ነቢያትን ይሰጥ እንደ ነበር፣ ሙሴ፣ ኢያሱና ሳሙኤል ምሳሌዎች ናቸው፡፡ ነገር ግን እስራኤላዊያን ሳሙኤልን፣ እንደ አህዛብ ንጉስ አንግስልን ባሉት ጊዜ ቅር ተሰኝቶ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ እግዚአብሔር የሰጠው መልስ፡-

“እግዚአብሔርም ሳሙኤልን እዲህ አለው፤

1ኛ ሳሙ 8፥7 “ንጉሣቸው እንዳልሆን የናቁት እኔን እንጂ አንተን አይደለምና ሕዝቡ የሚሉህን ሁሉ አድምጥ።”

በማለት ጥያቄያቸው ቢያሳዝነውም ፈቅዶላቸው በሚነግሰው ንጉስ ምርጫው ላይ ግን ራሱ ረድቷቸዋል፡፡ ምክንያቱም ለህዝቡ መልካም እንዲሆን ይፈልግ ስለ ነበር ነው፡፡ 1ሳሙ 8፡ 4-8

እግዚአብሔር የፖለቲካ መሪዎችን የሚሰጠው ለእስራኤል ብቻ ሳይሆን ለዓለም ሀገሮች ሁሉ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች አሉ፡፡ የዓለም ሕዝብ በሙሉ የእግዚአብሔር በመሆኑ ክርስቲያኖች በሌሉበትም አገር ቢሆን የአገር መሪ የሚሆኑ ሰዎች በመሾም ረገድ የእግዚአብሔር እጅ አለበት፡፡ ዘጸ19፡5-6

የግብጽ ፈርዖን በእግዚአብሔር ተሾመ፡- ሮሜ 9፡17 (ዘጸ 9፡14-16 ኃይሌን እንዳሳይህና ስሜም በምድር ሁሉ እንዲታወቅ ለዚህ አስነስቼኃለሁ)፣

የሶርያ ንጉስ አዛሄልን የሾመው እግዚአብሔር ነው፡- 1ነገ 19፡15-17፣

በእግዚአብሔር የተቀባ የጢሮስ ንጉስ፣- ኢሳ 45፡1-4፣ ኤር 27፡5-8፡፡

የባቢሎን መሪ፡- በታላቁ ኃይሌና በተዘረጋው ክንዴ ምድርን በላይዋ የሚኖሩትን እንስሳትና እጸዋትን ፈጥሬያለሁ፡፡ ለምወደውም እሰጣለሁ አሁንም እነዚህን አገሮች ሁሉ ለአገልጋዬ ለባቢሎን ንጉስ ለናቡከደነጾር እሰጣለሁ፣ ዳን 2፡20-21፤ 4፡24-26፤ 5፡18-20፤ መዝ 135፡5-6፡፡

ለሮማዊው መሪ፡- ከላይ ባይሰጥህ ኖሮ በኔ ላይ ስልጣን ባልኖረህ ነበር፣) ዮሐ 19፡10-11፣ ሰው ከላይ ካልተሰጠው በቀር አንዳች ሊቀበል አይችልም፣ ዮሐ 3፡27፣

እነዚህ የእግዚአብሔር ቃል ክፍሎች መንፈሳዊ ባልሆኑ የተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች ከአገራት ነገስታት ጀምሮ በመሪነት ስፍራ ላሉት ሁሉ ስልጣን የሚሰጠው እግዚአብሔር መሆኑን ነው

**በምድር ነገስታት ሁሉ ሹመት የእግዚአብሔር እጅ አለበት፡፡ ስለዚህ፡ -**

ለመንግስት ባለስልጣናት ክብር መስጠት- ለእግዚአብሔር መገዛታችንን (እርሱን ማክበራችንን) ከምገልጽባቸው መንገዶች አንዱ ነው፡፡ ሮሜ 13፡1-5-7፤1ጴጥ 2፡13-15-17፤ ቲቶ 3፡1-2

## ለሀገር መሪዎች አክብሮት መስጠት አተገባበር መንገዶች/ሁኔታዎች

1. በአቅራቢያችን ላሉ ሰዎች የመንግስት ባለስልጣናት ለሚያወጡዋቸው መመሪያዎች/ህግጋት በመታዘዝና በማድረግ መልካም ምሳሌ መሆን ነው፡፡ በእግዚአብሔር የተሾሙ ስለሆነ ከእነርሱ ጋር አቀራረባችንና ንግግራችንም በአክብሮት በትህትና መሆን አለበት፡፡ የተለያዩ ነገሮች ታክስ ክፍያም በአግባቡ መፈጸም፡፡

በፖለቲካዊውም አመራር ድጋፍ ለመስጠት በሚከፈቱ የውይይት መድረኮች ገንቢ አስተያየት/አዳዲስ ሀሳቦችን መስጠት ይቻላል፡፡ ክርስቲያን ስልጣን ለመያዝ መስራትም ይችላል፡፡ በልቡ የመሪነት ፍላጎት ካለው በመሪነት መስመር እንዲሰራ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን/ጥሪ እንዳለው ጠይቆ ማረጋገጫ ሲያገኝ አግባብ በሆነ መንገድ ቢመረጥ የሚሰራውን ዝርዝር ተግባር ማስተዋወቅና በተመራጭነት መወዳደር ይችላል፡፡

2. መሪዎቹ ከሚወስኑት ውሳኔ/ከሚሰሩት ስራ መካከል የማይስማማህ ሊኖር እንደሚችል አስቀድሞ ማወቅ፡፡ ባለስልጣናትን ማክበር ማለት በሚወስኑት ውሳኔ ሁሉ መስማማት ይገባል ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን በሚወስኑት ውሳኔ ተቃዋሚ ሆኖ በአደባበይ መዋጋት ተገቢ አይደለም፣ ፡፡ በሚወስኑት ውሳኔ ሁሉ በሚሰሩት ስራ ሁሉ እግዚአብሔር ይስማማል ማለትም አይደለም፡፡ በእግዚአብሔር ተሹመዋል ማለት ደግሞ የሚሰሩት ስራ ሁሉ እንደ አግዚአብሔር ፈቃድ ነው ማለት አይደለም፡፡ በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን የተገባቸውን ክብር መስጠት ግን የግድ ነው፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ያከበረውን ማክበር ስላለብን፡፡ ሌላው ምክንያት "እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን የቃወማል ለትሁታን ግን ጸጋን ይሰጣል፤" ስለሚል ባለሥልጣናት በንቀት ማየት፣ በእግዚአብሔር ፊት መታበይ እንዳይሆንብን ነው፡፡

ነገር ግን ባለስልጣናትን እንቢ የምንልበት አንድ ጉዳይ አለ፡፡ ይኸውም የእግዚአብሔር ፈቃድ የሆነውን ተግባር አታድርጉ ሰንባል አይሆንም ማለት ነው፡፡ ሐሥ 4፡19-20፤ 5፡29

3. አህዛብ እንደሚያደርጉት በእነርሱ ላይ በተቃዋሚነት ከመነሳትና ከተቃዋሚዎቻቸውም ጋር ከመተባበር መቆጠብ፡፡ ነገር ግን በግል ገንቢ አሰተያየት መስጠት የሚቻልበት ሁኔታ አፈላለጎ ማከናወን ይቻቻል።
   ምሳ 24፡21-22፣ በእግዚአብሔርና በንጉስ ላይ ከሚያምጹት ጋር አትተባበር፣ መክ 10፡20፣ በሀሳብ እንኳ (በንግግርና በሰው ፊት ቀርቶ) ንጉስን አትንቀፍ/አትማ፤

ኢሳ 8፡11-13 እግዚአብሔር ብርቱ እጁን በላዬ አድርጎ የእነዚህ ሰዎች ምክር እንዳልከተል አስጠነቀቀኝ፡፡ እንዲህም አለኝ፤ እነዚህ ሰዎች አድማ ብለው የሚጠሩትን ማንኛውም ነገር አድማ አትበሉ፡፡ …

1ሳሙ 8፡1-7፣ የእስራኤል ነገዶች ሽማግሌዎች ወደ ሳሙኤል ቀርበው እንደ ሌሎች ህዝቦች ሁሉ የሚመራን ንጉስ አንግስልን እንዳሉት፤ በተለያዩ ጉዳዮች እንደ ዓለማውያን መምሰል የሚያምረን ጊዜ እንዳይኖር መጠንቀቅ መልካም ነው፡፡

4. **ለሐገር መሪዎች ስለ መጸለይ፤ ለምን ለሐገር መሪዎች መጸለይ አስፈለገ?**

ሀ. ምሳሌ 21፡1 የንጉስ (የማንኛውም ባለስልጣን) ልብ በእግዚአብሔር እጅ ነው፡፡ እርሱም እንደ ቦይ ውሃ ደስ ወዳሰኘው ይመራዋል፡፡ (መልካም ወደ ሆነው እንዲመራቸው መማጸን)

ለ. 1ጢሞ 2፡1-2፣ ለራስህና ቤተሰብህ ላገርህም ህዝብ ሁሉ መልካም እንዲሆን፡፡ መሪዎች እግዚአብሔርን ሲበድሉ ቅጣት የሚጀምረው በመሪው ስር ካለ ህዝብ ነው፡፡ ቅጣቱ ድርቅ፣ የምድር መንቀጥቀጥ፣ ጦርነትና ስደት/መፈናቀል፣ የዋጋ ንረት...ወዘተ ሲሆን ቀድሞ የሚጎዳው ከታች ያለው ህዝብ ነው፡፡ ምሳሌ፡- ዳዊት የህዝብ ቆጠራ ባደረገ ጊዜ የደረሰው 2ሳሙ 24፡15፡፡ ተመሳሳይ ችግር እንደይደርስ እስራኤላዊያን ተሰደው ለሄዱበት ከለዳዊያን ምድር እንኳን ጸልዩ ተብለዋል፡፡ ኤር 29፡7

የጸሎት አርእስት ሊሆኑ ከሚችሉት ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል፡ -

1. እግዚአብሔር ራሱ አዲስ የሚመረጡትም ሆነ በሽግሽግ የሚተኩትን መልካም አስተዳደር የሚያሰፍኑትን፣ ሰው ያላወቀቸውም ቢሆኑ እንዲታወሱና እንዲመረጡ እንዲያደርግ፡፡ ዘዳ 17፡15፣ 1ሳሙ 16፡7፣ 12፤ (እግዚአብሔር አንድን መሪ የሚመርጠው ሰውየው ፍጹም ጻድቅ ስለሆነ አይደለም፡፡ ካሉት መካከል የተሻለ ሆኖ ያገኘውን ነው እንጂ 1ሳሙ15፡27-28፡፡ አንዳንዱን መሪ የሚያስነሳው ደግሞ በዚያች አገር ውስጥ እግዚአብሔር ያለውን አንድ ዓይነት ዓለማ ለማስፈጸም ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ የግብጹን ፈርዖን እስራኤላዊያንን የባርነት ቀንበር ስላበዛባቸው ወደ እግዚአብሔር ጮሁና ከባርነት ነጻ አወጣቸው፡፡
2. የእግዚአብሔርን ቃል ሁሌ እየተማረ በመጠበቅ፤ ለእግዚአብሔር ፈቃድ የሚገዛና ራሱን ከሌሎች ወገኖቹ የተሻለ አድርጎ በመቁጠር የማይታበይ እንዲሆን 1ነገ 2፡1-4፤ ዘዳ 17፡17-20፤ 1ሳሙ15፡12 የሚሰራው ለህዝቡ ጥቅምና ለእግዚአብሔር ክብር እንጂ እንደ ሳኦል ለራሱ ክብርና ሐብት ለማካበት እንዳይሆን፡፡
3. የአመራር/የመልካም አስተዳደር ጥልቅ እውቀትና ማስተዋል እንዲሰጣቸው ምሳ 28፡16፤ 1ነገ 3፡9፣ ንጉስ ሰለሞን በፊት ያልነበረው የማስተዳደር ዕውቀትና ጥበብ በመለመኑ ተሞላ፡፡ መክ10፡16 ብስለት ያላቸው እንዲሆኑ፡፡ ፍትሃዊ የሀብትና የልማት ስራ ክፍፍል በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች የሚያሰፍኑ፤ የድሆችን ጭቆናና የተለያዩ ችግሮች የሚየስቡና የሚያቃልሉ እንዲሆኑ መጸለይ፤ መዝ 72፡1-4
4. በተለይ ከበድ ያሉ ውሳኔዎች ወስነው ተግባር ላይ ከማዋላቸው በፊት የእግዚአብሔርን ምክር/ምሪት እንዲጠይቁ፡፡ እግዚአብሔርም የተናገራቸውን ሳያጓድሉ የሚፈጽሙ እንዲሆኑ፡፡ 1ሳሙ 15፡7-9፤

5. በመሪዎች ላይ አዎንታቀዊ/አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ክፍሎችን በተመለከተ፡-

ከመሪው ጋር አብረው የሚሰሩ ከፍተኛና መካከለኛ ባለስልጣናት እንዲተባበራቸው/ሁሉም ገንቢ ሃሳብ አመንጪ እንዲሆኑ፡፡ እርስ በርሷ የምትከፋፈል መንግስት አትጸናምና፡፡ 1ዜና 29፡23-24፤ ማቴ (መውጣት የሌለበት መረጃ ላልተገባ ክፍል የሚይሰጡ፣ መሪው በሚሰራው መልካም ስራ በሚያቀርበው መልካም አሳብ የሚስማሙ አጋሮች እንዲሆኑት)

- የሐገርን መሪ የሚያሳስቱት አብረውት የሚሰሩት ብቻ ሳይሆን ሕዝቡም ሊሆን ይችላል፡፡ የእስራኤል ህዝብ አሮንን ጣኦት ስራልን አሉት፡፡ 1ሳሙ 15፡24 ሳኦል ከእግዚአብሔር ይልቅ አብሮት የወጣውን ህዝብ ሰምቶ ግደል/አጥፋየተባለውን ማርኮ አመጣ፡፡ ዳዊት ግን ለዚህ ዓይነቱ አብረው ላሉ ሰዎች ክፉ አሳብ የሰጠው ምላሽ እግዚአብሔርን የሚያስደስት ነበረ 1ሳሙ 30፡21-25
- ክፉ አማካሪዎችን ለምሳሌ ከክፉ መናፍስት ጋር ቁርኝት ያላቸው አማካሪዎችና፤ ክፉ አመለካከት የተጠናወታቸውን እግዚአብሔር እንዲያርቅለት፡፡ መሪዎችም ክፉ መካሪዎችን የማይቀበሉ እንዲሆኑ፡፡ ምሳ 15፡22 ምክር ሲጓደል እቅድ ዕቅድ ይፋለሳል፤ በብዙ ምክር ግን ይሳካል፣ 24፡6 ጦርነት ለመግጠም መልካም ምክር ድል ለማድረግም ብዙ አማካሪዎች ያስፈልጋሉ ፡፡
  1ነገ 12፡1-11-19፣ የንጉስ ሰለሞን ልጅ ሮብአም ሁለት አይነት ምክር የሰጡ ክፍሎችና ውጤቱ የአገር መከፋፈል አስከተለ፤
- የትዳር ጓደኞች፡- ንጉስ ሰለሞን ያገባቸው ከአህዛብ የሆኑ ሴቶች አሳቱት፤ ደሊላም ለሳምሶን መውደቅ ምክንያት ሆነች፡፡
- የደህንነት ሰዎቻቸው ያልተገባ መረጃ በማቅረብ፣ የተገባ መረጃን በመደበቅ እንዳያዛቡ፡
- የውጭ ኃይሎች ራሳቸው የሚፈልጉት አሳብ የማይፈጽም መሪ በተለያየ መንገድ ሊያስወገወዱት የሚሰሩበት ጊዜ አለ፡፡ 2ሳሙ 5፡17 እግዚአብሔር የሕዝብ  አገልጋዮችን ሲቀባ የክፉት ወገን ደግሞ ውጊያ ያስነሳል፡፡ እግዚአብሔር እንዲዋጋላቸው መጸለይ፡፡
- ቤተክርስቲያን፡- በጸሎት፤ ከእግዚአብሔር ምሪት ሲቀበሉ ደግሞ በተቻለ መጠን ለመሪው በግል በመንገር ማገዝ፡፡

**ለቤተክርስቲያን መሪዎች የሚሰጥ ክብር፡ -** ዕብ 13፡17፤ 1ተሰ 5፡12-13፤ 1ጢሞ 5፡17-19፡፡ በአገራችን ብቻ ሳይሆን በዓለም ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የሚደረግ እንክብካቤና ክፍያ አነስተኛ ነው፡፡ አንዳንዶች ደግሞ ያለምንም ክፍያ የሚያገለግሉ አሉ፡ ፡ ከጥቂቶች በቀር የአብዛኞቹ መሪዎችና አገልጋዮች ኑሮ አስቸጋሪ ሁኔታ ላይ ነው ያለው፡ ፡ ሆኖም የእግዚአብሔር ጥሪ ስለደረሳቸው ለእግዚአብሔር ህዝብ መታነጽ ይደክማሉ፡፡ ስለዚህ ስራቸው ውጤታማ ሆኖ መልካም ፍሬ/የባህርይ ለውጥ እንዲያዩ ከመስራት ጀምሮ አቅም በፈቀደው ሁሉ አስራት ሳያቋርጡ በመክፈል መባና የመሳሰሉትን ስጦታዎችን በመስጠት መደገፍ/ማክበር ይኖርብንናል፡፡

**የሥራ ኃላፊዎችን ማክበር፣** ኤፌ 6፡5-7፤ ቆላ 3፡22-25 1ጴጥ 2፡18፤ 1ጢሞ 6፡1-2፤ ቲቶ 2፡9-10

**ወላጆችን ማክበር፣** ኤፌ 6፡1-4፤ ዘጸ 20፡12

**በእድሜ የሚበልጡ ሰዎችን** 1ጢሞ 5፡1-2፤ አረጋዊውን ሰው እንደ አባትህ ቆጥረህ ምከረው እንጂ በኃይል ቃል አትናገረው፡፡ ሌዋ 19፡32፤ 1ጴጥ 5፡5 ጎልማሶች ሆይ እናንተም ለሽማግሌዎች ተገዙ **እርስ በርስ መከባበርና ለሰው ሁሉ ክብር መስጠት**፤ ኤፌ 2፡3፣ 5፡21፡፡ **በባልና ሚስት መካከል መከባበር**፣ ኤፌ 5፡22-33፤

በአጠቃላይ ሰውን ሁሉ ማክበር የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፡፡

©ኤልያስ ታሪኩ (ዶ/ር) 2018 ዓ.ም.